# ጎጂ ባህሎቻችን (የመጨረሻው ክፍል)

*በተክሉ አባተ*

በዚህ የመጨረሻ ክፍል ከአስተሳሰባችንና ከአመለካከታችን ጋር ቀጥታዊ ግንኙነት አለው ብዬ የማስበውን ጎጂ ባህል አቀርባለሁ:: ይህን ጎጂ ባህል በሚገባ መመርመርና ማስወገድ ከቻልን አገራችን ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ሁለንታዊ ችግሮችና ቀውሶች ለመላቀቅ የሚያስችላትን ትክክለኛ መንገድ ልትይዝ ትችላለች:: ቀጣይነት አስተማማኝና ሁሉን አቀፍ የሆነ የእድገታዊ ለውጥ መሰረት ሊጣል ይችላል:: ነገር ግን ይህን ጎጂ ባህል ተቋቁሞ ማለፍና ለቀጣይ ብሄራዊ ለውጥ መስራት ፈታኝ እንደሆነ ግልጽ መሆን አለበት:: ይህን ጎጂ ባህል አጠር አድርጌ ከገለጽኩ በኋላ መፍትሄ ጠቋሚ ሃሳቦች ላይ አተኩራለሁ::

## የሥርዓት ለውጥ ባህላችን

የአገራችንን የሩቅና የቅርብ ታሪክ ስናነብ ጎልቶ የሚታይ ሃቅ አለ:: ኃይል የሥልጣን ሁሉ መገኛ ማግኛና ማቆያ መሆኑ:: ይህ ሃቅ ሁሉንም መንግስታት በደንብ ይገልጻቸዋል:: ሌላው ቀርቶ ሰለሞናዊ ሥርዎ መንግስት በሰላም እንቀባበላለን የሚሉ ንጉሳዊ ቤተሰቦች ሳይቀሩ በዚህ መንገድ መሪያቸውን ሲያስቀምጡ ኖረዋል:: የሰው ደም ሳያፈስ የነገሠ ንጉሥ የለም:: ሥልጣን ሊቀናቀን ይችላል ተብሎ የተገመተ በአጭሩ ሲቀጭ ኖሯል::

ከዚያም ደርግ በጊዜው የነበረውን የህዝብ ብሶት ምክንያት በማድረግ ኃይል ተጠቅሞ ጃንሆይን ከመንበራቸው አወረደ:: በስንት ድካም ኢትዮጵያ ያፈራቻቸውን ሚኒስትሮችና ሌሎች ባለሥልጣናትን በጥይት ደብድቦ ገደላቸው:: ሌላው ቀርቶ ደርግን የመሰረቱት ቁልፍ ሰዎች ሳይቀሩ እየተመረጡ "አብዮታዊ እርምጃ" ተወሰደባቸው:: በዚህ ሁኔታ ይህ ኃይል ያለው አካል ለ17 ዓመታት ኢትዮጵያን አስጨንቆ ገዛት:: በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ደመ ከልብ ሆነው ቀርተዋል::

ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ የመቆያ ጊዜ አለውና ደርግን ሌላ ኃይል ተካው:: "ብሶት የወለደው ጀግናው የኢሕአዴግ ሠራዊት" እስከአፍንጫው የታጠቀውን የደርግ ሠራዊት ድባቅ መታ ተባለ:: የኢትዮጵያ ህዝብ አውንታዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ ጓጓ:: ይህ ጉጉት ብዙም ሳይቆይ ከሰመ:: ይህ መንግስትሥልጣን ላይ እያለ ኃይል ፍቱን ዘዴ እንደሆነ ደጋግሞ አሳየን:: ህዝብ ያልተሳተፈባቸውና ያልወደዳቸው ህጎችና ፖሊሲዎች ተረቀቁ:: ህዝብ በቋንቋና በዘር መስመር እንዲጓዝና ሁሉንም ነገር ከዚያ አኳያ እንዲተረጉም ተደረገ:: ትችት ያቀረቡና የተቃወሙ የኃይል ሰለባ ሆኑ:: በርካቶች የምድር ሲኦል በሆኑ እስር ቤቶች ተቆለፈባቸው:: ሌሎች ብዙዎች ወደባዕድ አገር ተሰደዱ:: ብዙዎች ተደበደቡ ተገደሉ:: ኃይል ያልገታው ምንም ነገር የለም:: በምርጫ ውስጥ ሳይቀር ኃይል አለ:: ኃይል ስላለ መንግስት ከፉኛ የተዳከመበት ምርጫ ሳይቀር እንዳልሆነ ሆነ::

ባጠቃላይ ሲታይ መሪዎቻችን ሥልጣን በኃይል ሲይዙ ኖረዋል:: የሚያስፈራቸው ነገር ቢኖር ኃይል ያለው ሌላ አካል ብቻ ነው እንጅ ህዝብ አይደለም:: አብዝተው የሚጨነቁት ለህዝቡ ለውጥና እድገት እንዴት መምጣት እንዳለበት ሳይሆን ተቀናቃኝ ኃይልን መምታት ላይ ነው:: እንደፈሪሳውያን ራሳቸው የማያከብሩትን ህግ እየጠቀሱ በነጻነት የሚያስቡና የሚናገሩትን ያድናሉ:: ይህ ባህል ማኅበራዊ ባህላዊ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሃብታዊ እድገት እንዳይመጣ ከማድረጉም ሌላ በምንም የማይተካውን የሰው ልጅ ህይወትን ቀጥፏል:: በነጻነት ቀና ብሎ የመኖር ጸጋን ገፏል:: ምንም እንኳን በብሄራዊ ደረጃ በማንም ቅኝ ያልተገዛንና ነጻ ብንሆንም በመሪዎቻችን ወጠምሻ ጡንቻዎች ስንታሽ የኖርን ባሪያዎች ግን ነን::

## ጦርነት ወይስ ምርጫ?

ሁለንታዊ እድገታዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው እንዴት ነው ተብለን ብንጠየቅ መልሳችን ከሁለት አንዱ ላይ ያርፋል:: ሰላማዊ በሆነ መንገድ ታግሎ በምርጫ መንግስትን ማሸነፍ እንደሚቻል የሚያምኑ አያሌ ናቸው:: አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን መስመር ተከታይ ናቸው:: እሾህን በእሾህ እንዲሉ ጦርነት በመንግስት ላይ በማካሄድ ለውጥ ይመጣል ብለው የሚያምኑ በየጫካውና በየረሃው የሚማስኑ አሉ:: የትኛው መንገድ አትራፊ እንደሆነ መናገር እጅግ ከባድ ነው:: ነገር ግን

ታሪካችንንና አመክንዮን ከግምት ውስጥ በማስገባት እነዚህን አማራጭ መንገዶች መገምገም እንችላለን:: ለኢትዮጵያ ***ሰላማዊ ዘለቄታዊና ፍትሃዊ ለውጥ*** (ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ማለቴ ነው) ማምጣት የሚያስችል አቅጣጫ መጠቀም ይቻላል::

እኔ ግን የመጀመሪያው መንገድ (በምርጫ ማሸነፍ) በፍጹም እውነተኛ ለውጥ አያመጣም ብዬ አምናለሁ:: በምርጫ መሸነፍ ሥልጣን ላይ ላሉ ግለሰቦች ቀጥታዊ አስጊ ሁኔታ ሊፈጥ ይችላል:: ብዙ ባለሥልጣናት በተለያዩ ወንጀሎች ሙስናን ጨምሮ የተሳተፉ ናቸው:: ከተሸነፉና ሥልጣን ከለቀቁ ለፍርድ እንደሚቀርቡ ወይም በቀል እንደሚፈጸምባቸው ያምናሉ:: በጀንሆይና በደርግ ባለሥልጣናት ላይ የተደረገውን በማሰብ ከተመሳሳይ ጥቃት ሊድኑ የሚችሉበትን መንገድ ይከተላሉ:: በሰላም ቀሪ ህይወታቸውን መምራት እንደማይችሉ በመገመት ያለ የሌለ ኃይል ተጠቅመው ሥልጣን ላይ መቆየት ይመርጣሉ:: ምርጫን ለማሸነፍ በህዝብ ገንዘብ ፕሮፓጋንዳ ይሰራል:: አበል ለመራጩ ይከፈላል:: ሌላ ፓርቲ ሊመርጡ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዎች ማስፈራሪያና ዛቻ ይደርስባቸዋል:: ይህ ሁሉ ተደርጎ ገዥው ፓርቲ ቢሸነፍ እንኳን የህዝብ ድምጽ ይሰረቃል:: ሥልጣን አለቅም ማለት ይመጣል:: የ1997ቱ ምርጫ ለዚህ ሃተታ ህያው ምስክር ነው:: በመሆኑም ባለሥልጣናትን ጭምር ነጻ የሚያወጣ የፖለቲካ መፍትሄ እስካልተገኘ ድረስ በምርጫ ማሸነፍ ይቻላል ብሎ ማሰብ የህልም እንጀራ ነው::

ጦርነትም ቢሆን ዘለቄታነት ያለው ሁሉን አቀፍ ለውጥ ያመጣል የሚል እምነት የለኝም:: በዘመናችን ያሉትን ከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ መንግስትን በኃይል ማሸነፍ ቢቻል እንኳን ሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው አስጊ ሁኔታ እንደተፈጠረባቸው ያስባሉ:: አሸናፊው ኃይል አራት ኪሎ ሲገባ እነሱ ወደበረሃ የሚገቡበት አጋጣሚ ይኖራል:: ይህም ባይሆን ወደምዕራቡ አገራት መሸሽና ከዚያ ሆኖ ትግል መጀመር የተለመደ ነው:: በተጨማሪም በኃይል የገባ እስካሁን እንዳየነው በቀላሉ ሥልጣን ሊለቅ ወይም እውነተኛ ዴሞክራሲ ሊያሰፍን ይሳነዋል:: ሲደመር አሁን ያለንበት ወቅት ዘርን ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ደጋፊ ነው:: በመሆኑም በጦርነት የሚገኝ ፖለቲካዊ ድል በአንድ ብሄር ላይ የተገኘ ድል መስሎ ሊታይ ይችላል:: ይህም መራራ ብጥብጥና  ቀውስ ይፈጥራል:: የአንዳንድ ብሄረሰቦችን የመገንጠል እድልን ያሰፋል:: መገንጠሉ ደግሞ  የራሱ ምስቅልቅሎች አሉት:: ከተገነጠሉም በኋላ በድንበርና በሃብት የተነሳ ወደጦርነት የመግባት እድሉ ሰፊ ነው:: ለዚህ ኤርትራ ጥሩ ምሳሌ ናት:: ሌላው ጦርነትን ያህል ጎጅ ባህል ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ  ለጎሊና የማይመች ነው:: ምንም ይሁን ምን በጦርነት የሚመጣው ለውጥ እጅግ መስዋዕትነት የበዛበትና ጊዜያዊ ነው የሚል እምነት አለኝ::

## ሦስተኛው  መንገድ

ጦርነትና ምርጫ ሁሉን አቀፍና ዘለቄታዊ ለውጥ የማያመጡ ከሆነ መፍትሄው ምንድን ነው? ለብሄራዊ መግባባት ከዚያም እርቅ የሚያበቃ ክርክርና ውይይት ማካሄድ መፍትሄ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ:: ይህ መንገድ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ አማራጮች ቀጥለው በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሳ እጅጉን የተሻለ ነው::

- ይህ መንገድ በሚገባ ከተያዘና ከተጠናቀቀ አምባገነኖችን ሳይቀር ነጻ የሚያወጣ ነው
- ይህም በመሆኑ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምስረታ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ
- ሁሉም ተሳታፊ ስለሚሆን ጦርና የጦር ወሬዎች ታሪክ እየሆኑ ይሄዳሉ
- ይህ መንገድ የሰው ህይወትም ሆነ ንብረትና ሃብት አያጠፋም በመሆኑም ይህ የፖለቲካ መስመር ጭስ አልባ ሊባል ይችላል
- ስለሆነም በሚያስፈራ ዝምታ ውስጥ ያለውን የሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ቀልብ ሊስብ ይችላል
- ለመግባባትና ለእርቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ስላለው አስፈላጊውን ድጋፍና ማበረታቻ ማግኘት አይከብድም
- በመጨረሻም ይህ የትግል ስልት ቀጣይነት ያለው ሰላምና እድገት ለኢትዮጵያ ያስገኛል

## አመቺ  ሁኔታዎች አሉ?

ብዙዎች ይህን ሦስተኛውን የፖለቲካ ስልት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ይደግፋሉ:: ዳሩ ግን እርቅ ለማካሄድ አስገዳጅ ወይም አመቺ ሁኔታዎች የሉም ሲሉ ይሞግታሉ:: የተወሰነ እውነታ ሊኖረው ይችላል:: ነገር ግን አመቺ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው

ብለን መጠየቅ ይገባል:: ምን አይነትና ምን ያህል አመቺ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ? እኔ ግን ብሄራዊ እርቅ ለማድረግ ከበቂ በላይ ተፈላጊ ሁኔታዎች አሉ እላለሁ:: ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል::

- የገዥው ፓርቲ ሞተሩ አቶ መለስ ከሞቱ በኋላ ፓርቲው ጀርባውን እንደተመታ እባብ ክፉኛ እየተልፈሰፈሰ ነው
- ባለሥልጣናቱም በሙስና ተነከረዋል መውጫ በር ካገኙ አይናቸውን አያሹም
- ጣሪያ የነካ የኑሮ ውድነት ህዝቡን ክፉኛ አድቅቆታል ይህም ባለሥልጣናቱን አሳስቧቸዋል
- የኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች እውነት መናገርና መልቀቂያ ማስገባት ጀምረዋል
- የአመራሩ እድሜ መግፋትና የጤና መታወክ ለሰላማዊ ለውጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል የማታ እንጀራ ከሰላም ጋር የሚጠላ የለም
- የውጭ ምንዛሬ እጥረት የመንግስትን እንቅስቃሴ ገትቷል ቢዝነሶች እየቆሙ ነው
- የሃይማኖት ተቋማት በተለይ ኦርቶዶክስና እስላም በመንግስት ላይ ተቃውሞ ማሰማት ጀምረዋል
- ከ90% በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሃይማኖተኛ ስለሆነ ይቅርታ ለማድረግና በአንድነት ለመኖር አይከብደውም
- አገር ቤት ያሉ ተቃዎሚ ፓርቲዎች እምቢታቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል
- የታጠቁ ኃይሎች መንግስትን እያሳሰቡት ነው
- የምዕራባዊያን አንዳንድ መንግስታትና ተቋማት ሰብአዊ መብት እንዲከበርና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ እየጠየቁ ነው
- ዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ የመንግስት ባለሥልጣናት ውጭ አገር ሲወጡ አላንቀሳቅስ ብሏል ገንዘብ መሰብሰብ ቀርቶ ሻይ ቡና ማለትና መዟዟር አልቻሉም
- አምባገነኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊከሰሱበት የሚችል አጋጣሚ አለ ሃብታቸውም እንዳይንቀሳቀስ እየተደረገ ነውና ይህ ለባለሥልጣናቱ አስጊ ነው
- በአጠቃላይ የእነዚህና የሌሎች ሁኔታዎች ድምር መንግስት ሁሉን አቀፍና ጭስ አልባ ድርድር እንዲቀበል ያደርጉታል

ይህ ሦስተኛው የትግል ስልት እንዴት በማንና መቼ መጀመር እንደሚችል ከወራት በፊት የቀረበን ጽሁፍ ይህን በመጫን ያንብቡ http://tekluabate.blogspot.no/2013/07/inclusive-debate-prelude-to-national.html#more

**ማጠቃለያ**

በዚህ ጽሁፍ ሦስተኛ የተባለው ለውጥ ማስገኛ ዘዴ ከሌሎቹ ከተለመዱት የትግል ስልቶች የሚለየው ሁሉን አቀፍ ዘለቄታዊና አፋጣኝ እድገትን ሊያመጣ እንደሚችል በመታሰቡ ነው:: በሰው ልጅ ህይወትና በንብረት ላይ ምንም አይነት ውድመት አያመጣም:: ይህ መንገድ ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገባ አልተኬደበትም:: የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች እንዲሁም ሲቪክ ድርጅቶች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡት የሚገባ አማራጭ ነው:: ነገር ግን ከጦርነት ያላነሰ ርብርብና ስትራቴጅ ይፈልጋል:: በዋናነት የነገዋን ኢትዮጵያን እንጅ የዛሬዋንና የትናንትናዋን አይስልም:: ይህንም ለማድረግ ላቅ ያለ የሰብአዊነትና የሞራል ብቃትንና ብስለትን ይጠይቃል:: ይህን የለውጥ ስልት እንድንወያይበት ሳሳስብ ግን ሌሎች በመደረግ ላይ ያሉ ትግሎችን ማንቋሸሼ ወይም እንዲቆሙ መጣራቴ እንዳልሆነ አንባቢ ይረዳልኝ::

/////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////////

*ገንቢ አስተያየት ካለዎትበteklu.abate@gmail.com ይላኩ!*